## የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ልዩ የግዥ
## <u>አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 232/2013</u>

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተሰጠዉን ኃላፊነት ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ባቸዉን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በወቅቱና ደህንነቱ በተጠበቀ አኳኋን መፈፀም ያለበት በመሆኑ፣

ኤጀንሲው የደህንነት ተቋም ከመሆኑ አንፃር ለሥራ የሚያስፈልጋቸዉን በአብዛኛው ከውጭ አገር የሚገዙ ዕቃዎች ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ በተለየ ጥንቃቄ ማዛት ስላለባቸው፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 3 ቁጥር 2(ሀ) ለሚኒስትሩ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ልዩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 232/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

2.1 የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

ሀ) ኤጀንሲ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ነው፡፡

ለ) "የአባልነት ምዝገባ" ማለት ኤጀንሲው በድረ - ገጽ አማካኝነት የደንበኝነት አባልነት ክፍያ በመክፈል ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር ስምምነት በመፈፀም ልዩ ልዩ የኤሌክትሮኒክ ጽሑፎችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከሄድ ምዝገባ ነው፡፡

ሐ) "የአባልነት ምዝገባ ክፍያ" ማለት ኤጀንሲው በአባልነት ለመመዝገብ ስምምነት ሲፈፀም ለአቅራቢው የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

መ) "ልዩ ግዥ" ማለት ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ ለብሔራዊ የመረጃ መረብ ደህንነት ሥራ ዓላማ በኤጀንሲው የሚፈፀም የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ነው፡፡

ሠ) "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

ረ) በዚህ መመሪያ ወስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌደራል የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የሥራ ባህርይ አንፃር በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ላይ ለተመለከቱ ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ ለሚገባው ግዥዎች ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በኤጀንሲው የሚፈፀሙ ልዩ ግዥዎች

## 4. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሥልጣን

በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ረ" መሠረት ለመ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ከአንድ አቅራቢ ግዥ እንዲፈፀም ለመወሰን የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የሚከተለው ተጨማሪ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

4.1 ከመረጃ መረብ ወይም ከሌላ ምንጭ በሚገኝ መረጃ መሠረት ግዥያቸው በሚስጥር መፈፀም አለበት ብሎ የሚያምንባቸውን ለብሔራዊ ደህንነት ሚያጋጥ የሚውሉ መረጃ ማሰባሰቢያ ችሎታዎችና የኢንፎርሜሽን ኦፕሬሽን አቅሞች ለብሔራዊ የመረጃ መረብ ደህንነት ሥራ የሚውሉ የምክርና የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን፣ ከመረጃ መረብ ወይም ከሌላ አስተማማኝነቱ ከተረጋገጠ የመረጃ ምንጭ በሚገኝ መረጃ ላይ በመመሥረት የሚሠራ ሥራዎች ግዥ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ ከተመለከቱት የግዥ ዘደዎች ወስጥ አግባብነት አለው ብሎ ያመነበትን የግዥ ዘዴ በማጠቀም ግዥው እንዲፈፀም እንዲወስን፣

4.2 ለኤጀንሲው የደህንነት ሥራ የሚጠቅምና በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከታወቁ የምርምር ተቋማት የሚገኙ የምርምር ጽሑፎች ከመረጃ መረብ ምንጮች ለማግኘት የአባልነት ምዝገባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስፈላጊውን የአባልነት ምዝገባ ክፍያ በመክፈል አገልግሎቱን እንዲያገኝ፣

4.3 ለአገራዊ የደህንነት ሥራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን ከምንጫቸው መግዛት ወይም በሶፍትዌሮቹ የመጠቀም መብትን እንዲያደስ፣

4.4 በሚስጥር መፈፀም አለባቸው ብሎ የሚያምንባቸው የምክርና የቴክኖሎጂ ወጠቶሀት ቀጥታ ከምንጩ ወይም ሌላ ተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቅሞ እንዲገዛ እንዲወስን፣

4.5 ከታወቁ ዓለም ዐቀፍ የምርምር ተቋማት ጋር የትብብር ስምምነት በማድረግ ተፈላጊ ሥራዎችን እንዲሠራ፣

4.6 ኤጀንሲው በተሰማራበት ዘርፍ አቅም ለማጎልበት የሚያስፈልጉ ሳይንቲስቶችና ኤክስፐርቶች ከማንኛውም የዓለም ክፍል አፈላልጎ ለመቅጠር፣

4.7 ለተለያየ ሥራዎች ጉዳይ ወደ ውጭ ሀገር በሚሄዱ ሁለት የኤጀንሲው ባለሙያዎች አማካይነት እያንዳንዳቸው በአንድ ጊዜ እስከ 10,000 (አሥር ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ዋጋ ያላገዘው የደህንነት መሣሪያዎች ከማንኛውም ቦታ እንዲገዙ የመፍቀድ፣

4.8 ለተጠቀሱት ግዥዎች አፈፃፀም የኤሌክትሮኒክስ የካርድ ክፍያ ዘዴ በማጠቀም ክፍያ እንዲፈፀም የመፍቀድ፣

## 5. <u>የልዩ ግዥዎች አፈፃፀም</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ሥር በተዘረዘረው መንገድ የሚፀሙ ግዥዎች ጥራታቸውን የጠበቁ እና ከወጣባቸው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ፋይዳ የሚያስገኙ ማሆናቸውን የሚጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

2. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ሥር ከተዘረዘሩት ወስጥ በተለይ ከንዑስ አንቀጽ 4.6 - 4.8 ለተጠቀሱት ግዥዎች ዕቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በማቅረብ ሚፀደቅ ይኖርበታል፡፡

3. ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ ለተዘረዘሩት ልዩ ግዥዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን የተለየ የወጪ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ይኖረዋል፡፡

## 6. <u>መደበኛ ግዥዎች</u>

ከላይ ከተጠቀሱት ወጪ ያሉ የኤጀንሲው ግዥዎች በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌደራል የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ይከናወናሉ፡፡

## 7. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የወጣው የኢንፎርሜሽን ሚብ ደህንነት ኤጀንሲ ልዩ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 8. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጥር 04 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 04 ቀን 2008 ዓ.ም

አብዱልአዚዝ ማሐመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር